# በልተኸው ተቀደስ

ምኒሊክ መስክ ላይ ፣ የበቀለው አረም
ሰደድ እሳት እንጂ ፣ አይፀዳም ቢታረም
   እሳት ነው መፍትሄው ፣ ተቆስቁሶ ይንደድ
   በጊዜ ማጥፋት ነው ፣ መመንጠር ስር ሳይሰድ
ወፍ ዘራሽ ለሆነ ፣ ሳይዘሩት ለወጣ
ከስሩ መንቀል ነው ፣ ዳግም እንዳይወጣ ።

ዛሬ የምትሰማቸው ፣ እነ ሁሉ ኬኛ
የጥፋት አበጋዝ ፣ የኦነግ ምርኮኛ
አይተው በማያውቁት ፣ ሰከረዋል ከፉኛ
እንዳያዘናጉህ ፣ አንተም እንዳትተኛ
   የጠገበ ሄዶ ፣ ጠኔያም ጅብ ሲመጣ
   ማግበስበስ ግድ ነው ፣ አያውቅም መረጣ ።

ኢትዮጵያዊነትን ፣ ጭራሽ የማያውቁ
ታሪካቸው ማፍረስ ፣ መገንባት አያውቁ
   አገር በቀል ድርቡሽ ፣ ማተብ የሌላቸው
   የባዕድ አጎብዳጅ ፣ መዋረድ ክብራቸው
በፈጠራ ታሪክ ፣ ዝቅታን ተላብሰው
በምናብ ድራማ ፣ ላይድኑ ቀውሰው
ታሪክ ሊገነቡ ፣ ታሪክን አፍርሰው
   ሁሌም ባጋጣሚ ፣ ዘመን ሲቀናቸው
   ሁከት እረብሻ ፣ ደም ማፍሰስ ምሳቸው
   ጥንትም ሆነ ዛሬ ፣ ይሄው ነው ገድላቸው ።

ሎሜ የመሰለህ ፣ አሳምሮ መልኩን
እንቧይ ነው ፣ ነገሩ ፣ አጣራ ታሪኩን
   ልብህን አትስጠው ፣ አትበለው ችላ
   ከበጎች መሃከል ፣ የገባ አለ ተኩላ
   አድብተውልሃል ፣ ከፊትም ከኋላ
በግራም በቀኝም ፣ ጠላት ሲሆን ወዳጅ
ቸል አትበል አንተም ፣ በፅናት ተደራጅ
   በንቃት ጠብቀው ፣ ታጥቀህ ዝናርህን
   ከፊት ብቻ ሳይሆን ፣ አስተውል ጀርባህን ።

እግር ያለው እባብ ፣ ቤተ መንግሥት ገብቶ
መተኛት ያቃተው ፣ በፍርሃት ተሞልቶ
ያንተን አረማመድ ፣ ጡንቻህን ለክቶ
ምቹ ቀን ጠብቆ ፣ ሊያጠፋህ አድብቶ
   የቆመ ጅብ አለ ፣ በልተኸው ተቀደስ
   ዳግም እንዳይለምደው ፣ ከደጅህ እንዳይደርስ ።

ታዛቢው

July 12, 2019